# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ክፍል አንድ ......................................................................1

*መግቢያ* ......................................................................1

*የኤጀንሲው ዓላማ፣ሥልጣንና ተግባር* ......................................................................2

*የክትትል ኦዲቱ ዓላማ፤*......................................................................4

*የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፤*......................................................................4

*የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርት፤* ......................................................................5

## ክፍል ሁለት ......................................................................6

*በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣* ......................................................................6

የፋይናንስ ብድር አቅርቦት እና አመላለስ አፈጻጸምን በተመለከተ......................................................................6

የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ፤ ......................................................................8

የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ፤ ......................................................................11

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ፤ ......................................................................14

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑን በተመለከተ፤......................................................................15

ኢንተርፕራይዞች ደረጃ ዕድገት ሽግግርን በተመለከተ፤ ......................................................................18

ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ፤......................................................................19

የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት በተመለከተ፤......................................................................20

የማምረቻ፣መሸጫና የገበያ ማዕከላት መጠቀሚያ የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ፤......................................................................22

ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜን በተመለከተ፤ ......................................................................24

የማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ድጋፍ በተመለከተ ፤ ......................................................................25

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ፤ ......................................................................26

## ክፍል ሦስት......................................................................29

*የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)*......................................................................29

*3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው፤*......................................................................29

*3.2፤ እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፤*......................................................................32

ክፍል አራት......................................................................................37

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)........................................................37

አባሪ አንድ ......................................................................................... 38

የተፈጠሩ ኢንተርፕራይዞች ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች መረጃ፤...............38

በዘርፍ እና ሽግግር ባደረጉበት አመት የሚያሳይ መረጃ.................................38

አባሪ 2 .......................................................................................... 39

የፌዴራል የከተሞችና የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ...............39

የተከለሱ ማስረጃዎች ዝርዝር ............................................................. 39

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፣ቀጣይነት ያለው፣ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሰረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን መደገፍና ማስተባበር፣ በከተማ ግብርና፣ በኮንስትራክሽን፣ በንግድ እና በአገልግሎት፣ በዕደጥበብ፣ በባህላዊ ማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍና በማሳደግ ተወዳዳሪ፣ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ የሥራ ዕድል በከተሞች እንዲፈጠር፣ የነዋሪዎች ገቢ እንዲሻሻል እና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የድጋፍ ማዕቀፍ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የደጋፍ ማዕቀፎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም፣

- የከተማ የሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸምን በተመለከተ ፣
- የከተማ ቁጠባና ብድር አገልግሎት አሠጣጥን በሚመለከት፣
- የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት፣
- የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓትን የሚመለከት፣
- የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር አፈጻጸምን መተመለከተ፣
- የጥሪት ማፍሪያ የሥራ መሰኮች አደረጃጀትና አሰራርን በተመለከተ፣
- የመስሪያና መሸጫ ሼድና የገበያ ማዕከላት የቦታ ዝግጅት፣ ዲዛይን፣ ግንባታ እና አስተዳደርን በተመለከተ፣
- የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

2. ይህንንም ከላይ የተገለጹትን ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 ዓ.ም የማቋቋሚያ ደንብ መሰረት ተቋቁሞ የነበረው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ሁለት ቦታ በመክፈል በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 374/2008 ዓ.ም የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ፤ሥልጣንና ተግባር

ዓላማ፡-

3. በሚኒስተሮች ደንብ ቁጥር 374/2008 መሰረት ሚከተሉት አላማዎች አሉት

- የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ መሥራት ለማይችሉ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት እየቻሉ ሥራ ለሌላቸው እና ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት በማሻሻል የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ፤
- የጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፤ቀጣይነትያለው፤ ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሰረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን መደገፍና ማስተባበር፤
- በጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ በከተማ ግብርና፤በግንባታ፤በንግድ እና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍና በማሳደግ ተወዳዳሪ፤ ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ የሥራ ዕድል በከተሞች እንዲፈጠር የነዋሪዎች ገቢ እንዲሻሻል እና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ
- የዜጎችን የተመጣጠነ የሥርዓት ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፡፡

ሥልጣንና ተግባር፤

4. በሚኒስተሮች ደንብ ቁጥር 374/2008 ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

  - የከተሞች ምግብ ዋስትናና የስራ እድል ፈጠራ ስራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ ስትራቴጅዎችን ይነድፋል፣ መረሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
  - የልማታዊ ሴፊቲኔት፣ የኑሮ ማሻሻያና የጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዉጭ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ድጋፍ ማእቀፎች ይቀርጻል፣ ያስተባብራል ፤አፈጻጸሙን ይከታተላ፤

- ለከተሞች ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ ለስራ እድል ፈጠራ እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሄ ይሰጣል፤
- የከተሞች ምግብ ዋስትናና የስራ እድል ፈጠራ የሚደግፉና የሚያስተባብሩ ተቋማት የድጋፍ ማዕቀፎችን አቅም ይገነባል፤
- የከተሞች ምግብ ዋስትናና የስራ እድል ፈጠራ ስትራቴጂ መሰረት በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- የእሴት ሰንሰለትንና የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዉጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ፍላጎት መሰረት በማድረግ ለጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዉጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ድጋፍ ሰጪ ተቋማት የሚያቀርቡትን የስልጠና ፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ያስተባብራል፤
- በማህረሰቡ ዉስጥ ያለዉን የተዛባ የስራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ስልጠና ስራዎችን በስፋት እንዲሰሩ የሚያግዝ የህዝብ ንቅናቄ በከተሞች እንዲፈጠር ድጋፍ የደርጋል፤
- የሚመለከታቸዉን አካላት በማስተባበር የከተሞች የማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ እንዲሁም ለህገወጥ የሰዎች ዝዉዉር ፍልሰት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የመከላከልና የተሃድሶ ስራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፤
- ከተሞችን በየፈርጃቸዉ ለማወዳደር የሚወጡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ምዘና እና የማወዳደሪያ መስፈርቶች ዉስጥ የከተሞች ምግብ ዋስትና ጉዳይ እንደ አንድ መስፈርት መካተቱን የከታተላል፤
- ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዉጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕታይዞች በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ ከሀገር ዉስጥ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የስራ እድል ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ስራ የሌላቸዉን፣ መስራት የሚችሉና የማይችሉ ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መረጃ በማጥናት በመለየት የሰበስባል፣ የተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤
- ከድህነት ወለል በታች ላሉት ተጠቃሚዎች የተለየ ፓኬጅ ቀርጾ ወደ ስራ ያሰማራል በጊዜ ገደብ እንዲመረቁም ያደርጋል፤

- ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናት በመቀመርና በማጥናት የከተሞች ምግብ ዋስትናና የስራ እድል ፈጠራ ስራዎችን ይተገብራል፤
- ተመሳሳይ አላማ ካላቸዉ የሀገር ዉስጥና የዉጭ ሀገር የግልና የመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፤
- የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣ ዉል ይዋዋላል ፣ በስሙ ይከሰሳል፣ ይከሳል ፤
- አላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናዉናል፤

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ፤

5. ቀደም ሲል በቀድሞው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ላይ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም ላይ በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶች እና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ ለአሁን የፌዴራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የሚመለከቱ ግኝቶች ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፤

6. የክትትል ኦዲቱ ወሰን በዋነኛነት የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተከናወነ ሲሆን በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ፤ በየካ ክፍለ ከተማ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት፤ በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም የየካ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽቤት፤ የአዲስ አበባ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም፤ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፤ አቦስቶ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ፤ የሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም፤ ሀዋሳ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ምስራቅ ቅ/ጽ/ቤት፤ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም የሀዋሳ ከተማ ዲስትሪክት ጽ/ቤት፤ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም መናህሪያ ቅ/ጽ/ቤት፤ የሀዋሳ ከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ዘርፍ፤ ለሚገኙ ለሚመለከታቸው የስራ ኃፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብና የድጋፍ ማዕቀፍን በተመለከተ የተዘጋጁ መመሪያዎችን፤ 2007-2010 እቅድና የእቅድ አፈጻም ሪፖርት፤ የተግባርና የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት አፈጻጸም የክትትል፤ የድጋፍና የሱፐርቪዥን ሪፖርት (2009-2001 የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ፤ የተከናወነ ሲሆን የክትትል ኦዲቱ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም ሩብ ዓመት ድረስ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸምን በተመለከተ

በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ እና ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የተደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርት፤

7. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

### የፋይናንስ ብድር አቅርቦት እና አመላለስ አፈጻጸምን በተመለከተ

8. ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሚደረገውን የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ድጋፍ በተመለከተ በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ አካቶ በማቀድ በየበጀት ዓመቱ እየተመነዘረ ተግባራዊ መደረግ አለበት፤

9. በኦዲት ወቅት የቀድሞው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

- በየዓመቱ ወደ ሥራ ለሚገቡ ለአዳዲስ ኢንተርፕራይዞች እና ነባር አንቀሳቃሾች የብድር አገልግሎት ለማመቻቸትና እንዲቀርብ ድጋፍ ለማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት ማድረጉ፣ ነገር ግን
- የብድር ስርጭት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ ከብድር ገንዘብ አቅርቦት አንጻር በዕቅዱ መሰረት ባይከናወንም አፈጻጸሙ በየጊዜው እየተሻሻለ መምጣቱ፤
- ከብድር ተጠቃሚዎች ብዛት አንጻር ግን አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የብድር መመሪያው የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራ ዕቅዱን/ የአዋጭነት ጥናቱን ለጽ/ቤት ባቀረቡ በ15 ቀናት ውስጥ ብድሩን እንዲያገኙ ይደረጋል ቢባልም በተጨባጭ ግን በተባለው ጊዜ ውስጥ የማያገኙ መሆኑ፤
- የተሰጠ ብድር አመላለስን በተመለከተ አበዳሪ ተቋሚት ላይ ወዝፍ ብድር እንዲኖርና ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን የ97% የብድር አመላለስ ምጣኔ መመሪያ እንዲሁም ኤጀንሲው ሲያቅድ የተሰራጨውን ብድር 100% መሰብሰብ እንዳለበት በግልጽ ቢያስቀምጥም ነገር ግን በየበጀት ዓመቱ የተሰራጨ ብድርን የማስመለስ አፈጻጸም ሲታይ በ2004 (69%)፣ 2005 (64%)፣ 2006 (75%) እና 2007 ዓ.ም (88%) እንደሆነ፤
- የብድር አቅርቦት ከኢንተርፕራይዝ ብዛት ጋር የማይመጣጠን መሆን፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር በተቀመጠላቸው የቆይታ ጊዜ ከፍለው ባለማጠናቀቃቸው ምክንያት የተጠራቀመ የብድር ውዝፍ እንዲከማች ማድረጉና
- የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ብድር ለመስጠቱ የሚተባበሩትን ያህል ማስመለስ ላይ ትብብራቸው አናሳ መሆኑ፣

በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

10. የፋይናንስና ብድር አቅርቦት በዕቅዱ መሰረት ሊከናወን እና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የብድር ፍላጎትን ያገናዘበ የብድር አቅርቦት ሊኖር እና ሥራቸው አዋጪ እስከሆነ ድረስ ብድሩን የሚፈልጉ ኢንተርፕራይዞች ሁሉ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማመቻቸት የብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞቹን ቁጥር ከፍ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

11. በኦዲቱ ወቅት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ኤጀንሲው ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

12. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፤ የብድር አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ እንዲቻል ከመደበኛ ብድር በተጨማሪ ሌሎች አማራጮችን መከተል አስፈላጊ መሆኑን ታምኖበት አስፈላጊው ጥናት እንዲጠና ተደርጎ በጥናቱ ግኝት ላይ ተመስርቶ

- በ2009 ዓ/ም የ10 ቢሊየን ብር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ እንዲመደብ መደረጉ፤
- ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ዘመናዊ የአሰራር ስርዓትን ለመዘርጋት የኮር ባንኪንግ ሲስተምን ለመጠቀም የተጀመረ ሥራ መኖሩ፣
- በየክልሎች የወጣቶች ተዘዋሪ ብድር ፈንድ በከተሞችና በገጠር ላሉ ለይቶ በመመደብና የተሰራጨውንም ብድር አፈፃፀም በገጠርና በከተማ ለይቶ ከማቅረብ አንፃር በትግራይ፤ በሀረሪ፤ በኦሮሚያና፤ በአማራ ክልል ችግር ያለ መሆኑ፣
- በፌዴራል ደረጃ ሞዴል የአሰራር መመሪያ በ2005 ዓ/ም በማዘጋጀት ለክልሎች ማውረድ የተቻለ ሲሆን ክልሎችም እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመቃኘት በክልላቸው/ ከተማ አስተዳደራቸው ካቢኔ በማፀደቅ በስራ መመሪያነት እየተጠቀሙ የሚገኙ ያሉ መሆኑ፣
- በአንፃሩ ከመነሻው ወደ ስራ ያልገቡ እና አሰራሩን ዘርግተው ወደ ስራ ያልገቡ ክልሎች መኖራቸው፤ አሰራሩን ዘርግተው አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት አማራ፤ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ በሂደት ያቋረጡበት ሁኔታ መኖሩ፤
- በአጠቃላይ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገለጽ የአሰራር ክፍተት ስለነበር ብሄራዊ ባንክ በውጭ አማካሪዎች በማስጠናት የመጀመሪ ረቂቅ

ቀርቦ አስተያየት ተሰጥቶበት መዳበር የቻለ ቢሆንም መመሪያውን አጽድቆ ወደ ክልሎች /ከተማ አስተዳደሮች የማሰራጨት ተግባር እስካሁን መፈፀም አለመቻሉ፣ በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ፤**

13. የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር እና በመደበኛ ባንኮች የተቀመጡትን የብድር ዋስትና/ማስያዣ (collateral) የማቅረብ አቅም ለሌላቸው ሥራቸውን ለመጀምር ወይም ለማስፋፋት የሚያስችል ብድር እንዲያገኙ ለማድረግ የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guarantee fund) በየክልል መንግስታት /በከተማ አስተዳደሮች መቋቋም አለበት፤ ኢንተርፕራይዞቹም የፈንዱን አላማ ምን እንደሆነ እንዲያውቁት የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት ኤጀንሲውም ክልሎች ፈንዱን እንዲያቋቁሙ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ አለበት

14. በቀድሞ ኦዲቱ ወቅት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በስተቀር የኦሮሚያ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የብድር ዋስትና ፈንድ አለማቋቋማቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በሰጡት ምላሽና በተሰበሰ መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው የከተማ መስተዳድሮች በራሳቸው ተነሳሽነት ለኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ሽፋን በመስጠት ብድሩ ቢመቻችም፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩት ገንዘብ በማስመለስ ሂደት ላይ መንግስት ዋስ ሆኖልናል በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ብድር ማስመለስ አለመቻሉ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

15. አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዞች ሥራቸውን ለመጀመርም ሆነ ለማሻሻል የሚስፈልጋቸውን የፋይናንስ አቅም እንዲያገኙ የሚያግዝ እና ለኢንተርፕራይዞቹ የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guarantee fund) በክልል መንግስታት/ በከተማ አስተዳደሮች ሊቋቋም ይገባል፡፡ በብድር ዋስትና ተጠቅመው የተበደሩ አካላትም የተበደሩትን ገንዘብ በውሉ መሰረት እየከፈሉ መሆኑ ጥብቅ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

16. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

17. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በፌዴራል ደረጃ የቁጠባና የፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ በማዋቀር በብሔራዊ ባንክ ሰብሳቢነት ኤጀንሲው በጸሀፊነት እንዲሁም አነስተኛ ማይክሮ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም ማህበር፣ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአባልነት የሚሳተፉበት ቴክኒክ ኮሚቴ የጋራ አቅድ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ መሆኑ፣
- በክልል ደረጃ 3ቱም ፈጻሚ አካላት ማለትም የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማትና የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ ያሉነት የቴክኒክ ኮሚቴ በማዋቀር በተቀናጀ መልኩ የድጋፍና ክትትል ስራ መሰራቱ፣
- ኢንተርፕራይዞቹ የወሰዱትን ብድር በገቡት ውል መሰረት እየከፈሉ መሆናቸውን በመረጃ የተደገፈ ክትትልና ድጋፍ ያለማድረግ፣
- አበዳሪ ተቋማት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በመገኘት ተገቢው አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው፣
- የ2010 ዓ/ም የ1 ሩብ አመት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እቅድ አፈጻጸምን መነሻ በማድረግ ለዘጠኙ ክልሎች ለ2 ከተማ አስተዳደር ከስራ እድል ፈጠራና ከኢንተርፕራይዞች ዘርፍ የተሰጠ ግብረ-መልስ ለመረዳት እንደተቻለው፣
  - የአማራ፣ ድሬደዋ፣ ሀረሬ ክልሎች የብድር ዋስትና ፈንድ በማቋቋም ወደስራ ያልተገባ መሆኑ፣
  - በመደበኛና በተዘዋዋሪ ብድር የተሰራጨ ብድር እንዲመልሱ ከማድረግ አንጻር የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም፣ የተሰጠ ብድር በተለይም በወጣት ተዘዋዋሪ ፈንድ የብደር ተጠቃሚ ዜጎች አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት አድርገውና ስለሚሰሩት ሥራ በቂ ግንዛቤ ወስደው ባለመደራጀታቸው ከፍተኛ የብድር አለመመለስ ችግር መታየቱና ይህም ደግሞ ለአዳዲስ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ድጋፍ አግኝተው ወደ ሥራ እንዳይገቡ እንቅፋት እየፈጠረ መሆኑ፣
  - ኢንተርፕራይዞቹ በጸደቀላቸው ቢዝነስ ፕላን መሰረት የወሰዱትን ብድር ላቀዱት ዓላማ እና በታቀደው ጊዜ ማዋል እንዳይችሉ የተቀናጀ ክትትል ድጋፍ ለማድረግ አለመቻሉ፣ተገምግሟል፡፡

18. በብድር አሰጣጥ ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ቅንጅት በማስመለሱ ወቅት የማይታይ መሆኑ፡ የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክተር የ2010 አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው በበጀት አመቱ ለወጣቶች የተሰራጨው ብድር መጠን ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻል-ጉምዝ ክልሎች እና የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ ስተዳደሮች ውጭ ሌሎች ክልሎች መረጃውን ለይተው ባለመላካቸው አፈፃፀሙ 29 %ብቻ መሆኑ፣

19. የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች ድጋፍ ክትትል ስራ ከተጠቃለለ ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው

    - ከተሞች የብድር አመላለስ ስርአት ከመዘርጋት አንጻር ሰፊ ክፍተት ያለ መሆኑ፣
    - በተለይ በአበዳሪ ተቋማትና በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ኢንተርፕራይዞች የብድር ተጠቃሚ ሲሆኑ ሙሉ የስራ አድራሻ፣ የተሰጠው የብድር መጠን፣ የእፎይታ ጊዜ፣ ብድር መመለስ የሚጀምሩበት ቀን፣ የሚመልሱት የብድር መጠን፣ ብድሩን መልሰው የሚጨርሱበትን ጊዜ ዝርዝር መረጃ በመያዝ የክትትልና ድጋፍ ስራው በቅንጅት እንዲሰራ ከማድረግ አንፃር በሁሉም ክልሎች ሰፊ ክፍተት ያለ መሆኑ ማረጋገጥ መቻሉ፣

- ለመመለስ አጠራጣሪ የሆነ ብድር ከ5% መብለጥ እንደሌለበት ክትትል እንደሚደረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ ታህሳስ 2009 ዓ.ም. የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ለጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች ካሰራጩት ብድር ለመመለሱ አጠራጣሪ የሆነ የብድር ምጣኔ 5.6 % ሲሆን ከተቀመጠለት ግብ ያለፈ መሆኑ
- የ2010 ዓ/ም የ1 ሩብ አመት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እቅድ አፈፃፀምን መነሻ በማድረግ ለዘጠኙ ክልሎች ለ2 ከተማ አስተዳደር ከስራ እድል ፈጠራና ከኢንተርፕራይዞች ዘርፍ የተሰጠ ግብረመልስ ለመረዳት እንደተቻለው የአማራ፣ የሀረሬ ክልሎች እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የብድር ዋስትና ፈንድ በማቋቋም ወደስራ ያልተገባ መሆኑ

20. በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ ብሔር ብሔሮችና ሕዝቦች፣ በአማራ፣ በሀረሪ እና በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች ከህዳር 18-29/2011 ድረስ የተካሄደ የ100 ቀናት ትግበራ እና የ2011 በጀት አመት ስራዎች አፈፃፀም ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት

- በአዲስ አበባ ከተማ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ የብድር አሰጣጡ ሲታይ ከክፍለ ከተማ ክ/ከተማ ልዩነት ያለው መሆኑና የስራ ዘርፎቹን ታሳቢ ያላደረገ መሆኑ፤
- በአማራ ክልል ከፌዴራል የተመደበው የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ያለቀ በመሆኑ ከብድር ተመላሽ ከሆነ ገንዘብ ለተወሰኑ ኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎቱ እየተሰጠ ቢሆንም በከፍተኛ ደረጃ የፍላጎትና የአቅርቦት አለመጣጣም በመኖሩ በጎንደር ከተማ ከ300 በላይ ኢንተፕራይዞች ተደራጅተው የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብደር ፈንድ በመጠባበቅ ወደ ስራ ለማሰማራት አለመቻሉ፤
- የፋይናንስ ድጋፍ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ለኢንተርፕራይዞች (አንቀሳቃሾች) የብድር ዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን፤
- የ2010 የዘጠኝ ወራት የጋራ እቅድ አፈፃፀም ላይ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የጋራ የመስክ ጉብኝት ለማካሄድ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ለማከናወን አለመቻሉን፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ፤

21. ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓለማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ መዘርጋት አለበት፡፡

22. በቀድሞ ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለመገንዘብ እንደተቻለው በስራቸው ትልቁ ችግር ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት ለነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር እንደማያውሉት እና ይህም ስለመሆኑ የሚከታተል ስርዓት በኤጀንሲዎችም (ጽ/ቤቶች) ሆነ በአበዳሪ ተቋማት የተጠናከረ ክትትል የማይደረግ በመሆኑ አንዳንድ ኢንተርፕራዞች አቅርበውት ከነበረው የሥራ ዕቅድ ውጪ የተበደሩትን ገንዘብ ለሌላ ስራ እያዋሉት መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

23. በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕርይዝነት ተደራጅተው የብድር ተጠቃሚ ለመሆን የሚያቀርቡት የሥራ ዕቅድ መሰረት የብድር ተጠቃሚ ከሆኑ በኋላ ኢንተርፕራይዞች

የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚከታተልበትና የሚያረጋግጥበት ስርዓት ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

24. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

25. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፣ መደበኛ የብድር ክትትል ፕሮግራም በማውጣት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሞያ የብድር ክትትል የማድረግ ስራ የሚሰሩ መሆኑ እና የብድርና ቁጠባ ተቋማትም ብድርም መከታተያ ፎርማት በማዘጋጀት ኢንተርፕራይዞችን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

26. 2009 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የጋራ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የተሰራጨ ብድር ለታለመለት አላማ መዋሉን መከታተልና በእቅድ የተያዘ ቢሆንም የተሰራጨ ብድር ለታለመለት አላማ መዋሉን ለመከታተል በፎርማቱ መሰረት ሪፖርት አጠናክሮ ለመላክ ቢታቀድም በእቅዱ መሰረት አለመከናወኑ፣

27. ቁጠባን በተመለከተ

- ይህንን ስራ በዋናነት የሚያከናውኑት ክልሎች ሲሆኑ በሰሩት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለካፒታል እቃ ፋይናንስ ድጋፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቀው 20 በመቶ ቅድመ ቁጠባ እንዲቆጥቡ በማድረግ ድጋፍ የሚደረግ ሲሆን፣ የስራ ማስኬጃ ብድር ለማግኘት የተቆጠበውን መረጃ እንደ ኤጀንሲ የመሰብሰብ ስራ አለመከናወኑ፣
- በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በአማራና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች ከሚያዚያ 8 እስከ ሚያዚያ 25/2010 የ9 ወራት ስራዎች ድጋፍና ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት መሰረት
    - የተሰራጨ ተዘዋዋሪ ብድር ማስመለስን በተመለከተ ሰፊ ክፍተት መኖሩ፣ ከብድር ስርጭት በፊት ለተበዳሪዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ አለመስራቱ፣ በምልመላ ሂደት ባለሀብቶችም ከጀርባው ተደራጅተው መገኘታቸው፣ ስራ ያላቸውና የሌላቸው ተደራጅተው መገኘታቸው፣ ከተደራጁና ብድር ከወሰዱ

በኋላ ተከፋፍለው የተበተኑ መኖራቸው፣ የተገዛላቸው የስራ እቃ የሸጡና የተበተኑ መኖራቸው፤

- ኢንዲስትሪዎች ለጠየቁት ብድር ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያሟሉ ለማድረግ ታቅዶ ያልተፈፀመ መሆኑ፣
- ቅድመ ሁኔታ ላሟሉ ኢንድስትሪዎች የስራ ማስኬጃ ብድር ለማሰራጨት ቢታቀድም ህጋዊ እውቅና ያላቸው ፤የንግድ እቅድ ወይም የአዋጭነት ጥናት የሚጠበቀውን ቅድመ ቁጠባ (20 በመቶ) በተመረጡ የሥራ ዘርፎች ላይ ለሚሰማሩ፤ የማምረቻ ቦታ (በክላስተር ማዕከላት፤ በግል ይዞታ ወይንም በኪራይ) ያላቸው፤የሦስተኛ ወገን የውል ስምምነት ያላቸው፤ የመልካም ተበዳሪነት ታሪክ ያላቸው ፤ሂሳባቸውን ያስመረመሩ እና የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ የሚችሉ ፤የወቅቱን ግብር የከፈሉ፤መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ተሟልቶ የሥራ ማስኬጃ ብድር መሰራጨቱን የሚገልጽ ማስረጃ በተፈለገው ሁኔታ ማግኘት ባለመቻሉ የሥራ ማስኬጃ ብድር መሰራጨቱን ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፤
- የ2009 ዓ/ም የተግባርና የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀምን ለመደገፍ በተደረገ ሱፐርቪዥን በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የብድር ውዝፍ መኖር
- እና ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የቅንጅታዊ አሰራር ክፍተት መኖሩ

ታውቋል፡፡

28. በተጨማሪም

- የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት መካከል ፌዴራል ቴክክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚንስቴር አባላት በተደጋጋሚ በሚጠሩ የኮሚቴው ስብሰባዎች ላይ አለመገኘት፣
- ባለድርሻ አካላትና ፈፃሚ ተቋማት ዕቅድን በሚገባ ተረድተው በባለቤትነት እና የመደበኛ የስራ እንቅስቃሴ አካል አድርገው በቁርጠኝነት ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ላይ ውስንነት መኖሩን፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል

### የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ፤

29. ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የስትራቴጂክ ዕቅድ በማውጣት በየዓመቱ በመመንዘር እየገነባ ለኢንተርፕራይዞቹ ማቅረብ አለበት፤

30. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት ግንባታቸው ተጠናቀው ሁለት ዓመት ቢያስቆጥርም ለኢንተርፕራይዞቹ እንዳልተላለፉ ከመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ5 ዓመታት ውስጥ ለመገንባት ከታቀዱት የሼድ፣ የህንፃና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ መሳካቱንና መሰረተ ልማት ሳይሟላላቸው ለብዙ ጊዜ የተቀመጡ የማምረቻና የመሸጫ ህንጻዎች እንዳሉ ኤጀንሲው የሚያውቅ መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

31. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት እና ሼዶች ግንባታ ለማካሄድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የሚገነቡት ማዕከላት ብዛት በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊታቀድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

32. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

33. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፤

- ለስራ እድል ፈጠራ እና ለኢንተርፕራይዞች ልማት በሚውሉ የመስሪና የመሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ መስጠት የሚያስችል ጥናት በ2010 ዓ.ም. በኤጀንሲው በኩል መጠናቱ፤
- በአምስቱ የእድገት ተኮር ዘርፎች ላይ በሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች የሚታዩ ችግሮችን ለመለየት በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ችግርን በሚመለከት የጥናት ሰነዱን መነሻ በማድረግ ከክልሉ የዘርፍ አመራሮች ጋር በታዩ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ የምክክር መድረክ የተዘጋጀ መሆኑ፤
- ክልሎች በእቅዳቸው ውስጥ የሼድ ግንባታ እንዲያካትቱ በማድረግ አስፈላጊው በጀት ተመድቦ ግንባታው እንዲካሄድ የድጋፍ ክትትል ስራው እየተሰራ መሆኑ፤

- በሁለተኛው ጂቲፒው በ5 ዓመት 15000 ሼዶችን ለመገንባት ታቅዶ በ3 ዓመት ወስጥ 19090 (127%) መገንባት መቻሉ፤
- ለማምረቻ ለመሸጫ ቦታዎች የሚገነቡት ለስራና ለገበያ ምቹ የሆነ አካባቢ ላይ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ውስንነቶች መኖር፣
- የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎችን ለመኖሪያነት እየተጠቀሙ ያሉ ሰዎች መኖራቸው፤
- አዲስ ሊገነባ ለታሰበው የክላስተር ማዕከላት የሚውል መሬት ዝግጅት ከሦስተኛ ወገን ነፃ ለማድረግ ከፍተኛ የበጀት ችግር ያጋጠመ መሆኑ፣
- በሃዋሳ ከተማ ሼዶች በእስታንዳርዱ መሰረት ስለመገንባታቸው በተመደበ ባለሞያ ክትትል ቢደረግም የክትትል መረጃው ተደራጅቶ እንዲያዝ አለመደረጉ፤
- የቦታ አቅርቦት ከፍላጎት ጋር ያልተጣጣመ መሆን የተገነቡትም ለገበያ ምቹ በሆኑ ቦታዎች ያልተገነቡ መሆናቸው እና ደረጃውን በጠበቀ ማቴሪያል ያልተገነቡ መሆናቸው፤
- የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የማምረቻና መሸጫ የሚመቻቹ ቦታዎች በጥንቃቄ ያለመምረጥ፤
- የስራ እድል ፈጠራና ለኢንተርፕራይዞች ልማት በሚውሉ የመስሪያና መሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶች ጥናት ሰነድ ላይ ለስራ እድል ፈጠራ እና ለኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውሉ የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎች የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ለመስሪያ ወይም ለመሸጫ የሚገነቡ ሼዶች እና ህንፃዎች ወይም የገበያ ማዕከላት በተቀመጠው ዲዛይን መሰረት መፈፀም ላይ በከተሞች የሚገኙ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚንስቴር፤ የማዘጋጃ ቤት፤ የመሬት ልማት ማናጅመንት ቢሮ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- በከተሞች የሚገኙ የከተማ የስራ እድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ(ቢሮዎች) ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸው ቅንጅት ዝቅተኛ መሆኑ፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑን በተመለከተ፤

34. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የከተሞችን ፕላን መሰረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት

በየማዕከላቱ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማት (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ፣) ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የጥበቃ ቤት አሟልተው እንዲገነቡ መደረግ አለበት፤

35. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ለመገንዘብ እንደተቻለው ከ2004 እስከ 2007 ዓ.ም ውስጥ ኤጀንሲው ተገንብተው ለማስተላለፍ ካቀደው የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሕንጻ ግንባታቸው ተጠናቆ ልዩ ልዩ መሰረተ ልማቶች (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የጥበቃ ቤት ባለመሟላቱ ለኢንተርፕራይዞቹ ያልተላለፉ መኖራቸውን፣ ለኢንተርፕራይዞቹ ተላልፈው ሥራ የተጀመረባቸው ማዕከላትም ቢሆኑ መሰረተ ልማቶቹ ሳይሟላላቸው እንደተላለፈላቸውና በዚህም ምክንያት እንደተቸገሩ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የተገነቡ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የግንባታ ጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

36. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት እና ሼዶች ግንባታ ለማካሄድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የሚገነቡት ማዕከላት ብዛት በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊታቀድ ይገባል፡፡ የሚገነቡትም ማዕከላት እና ሼዶች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት በማድረግ እና የየከተሞቹን ፕላን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መገንባት አለባቸው፡፡ ከማዕከላቱ ግንባታ ጋር አብረው መሟላት የሚገባቸው የመሰረተ ልማቶች (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የመጸዳጃ ቤት፣ የጥበቃ ቤት የመሳሰሉት ተሟልተው ሊገነቡ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

37. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

38. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው፡

- ለክልሎች መሰረተ ልማት ችግር ያለባቸዉን ሼዶች በመለየት በተላከዉ የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት እንዲልኩ በማድረግ መረጃዉን አደራጅቶ ለውሀና መስኖ ኢነርጂ ሚኒስቴር ደብዳቤ በመጻፍ ችግሩ እንዲፈታላቸዉ ጥረት መደረጉ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤት በኩል ለአንዳንድ ክልሎች በዲስትሪክታቸዉ አማካኝነት ችግሮች እንዲፈቱላቸዉ ደብዳቤ ተጽፎ ክትትል እየተደረገ መገኘቱ በሚደረጉ

ሱፐርቪዥኖችም ችግሮችን በመለየት በክልሉ የበላይ አመራሮች እንዲፈታ ግብረ መልስ መሰጠቱ፣

- በአምስቱ የዕድገት ዘርፎች ላይ ያሉ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት እንደታየው በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ አስ/የ01 ቀበሌ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢየ ለስራ ምቹ ባልሆኑ ቦታዎች የተገነቡና መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው ሼዶችና ክላስተሮች ያለስራ መቀመጣቸው፤
- ለአገልግሎት ዘርፍ የተሰሩት ሼዶችና ክላስተሮች አገልግሎት ለመስጠት ሽንት ቤት ስለሌላቸው በጤና ፅ/ቤት እየታሸጉ ኢንተርፕራይዞች መጉላላታቸው፤
- በኦሮሚያ ክልል በዱከም ከተማ አስተዳደር የ01 ቀበሌ የአ/ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው መሆኑ፣ በአሰላ ከተማ አስተዳደር የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፅ/ቤት የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ያልተጣጣመ መሆኑ፤ በሻሸመኔ ከተማ የተገነቡትና በመገንባት ላይያሉትም ለስራ ምቹ ያልሆኑና የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው መሆን ለአብነትም 01 ቀበሌ 64 ሼዶች በመሰረተ ልማት ችግር ወደስራ ያልገቡ መሆኑ
- በመብራት ችግር ወደ ስራ ያልገቡ የማምረቻ ሼዶች በተለያዩ ከተሞች በመኖራቸው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቅድሚያ ለመስጠት እንዲችል በመብራት ኃይል የጋራ እቅድ በማዘጋጀት እና በጋራ ለመገምገም መግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፤
- በኦሮሚያ፣ በትግራይ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች፣ በአማራ ፤በሀረሪ ክልሎች እና በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች ከህዳር 18-29/2011 ድረስ የተካሄደ የ100 ቀናት ትግበራ እና የ2011 በጀት አመት ስራዎች አፈፃፀም ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ከመስሪያ ቦታ ድጋፍ ጋር በተያያዘ ትልቁ ማነቆ የመሰረተ ልማት ችግር ሲሆን በታዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የችግሩ ስፋት ቢለያይም በአብዛኞች የተላለፉ ሼዶች የታዩ የመብራት፤የውሃ፤የመፀዳጃ ቤት ያለመሟላት ችግር መኖሩ፤በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለይም መብራት ባለመሟላቱ እና በትራንስፎርመር ችግር የተጠናቀቁ ሼዶች ለኢንተርፕራይዝ ለማስተላለፍ አለመቻሉ፤
- በመሰረተ ልማት ችግር ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ህንፃዎችና ሼዶች በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለመፍታት በማሰብ የተሰበሰበ

መረጃ ላይ እንደሚያመለክተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ በ2008/2009/2010 ዓ.ም ለቆጣሪ፤ መስመር ዝርጋታ እና ለትራንስፎርመር ማስገቢያ ጠቅላላ 35.304.340.07 ብር ለኢትዮጵያ ለኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተከፈለ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስተጠናቀቀ ድረስ የተገነቡት ህንፃዎችና ሼዶች የኤሌትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አለመሆናቸው፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ኢንተርፕራይዞች ደረጃ ዕድገት ሽግግርን በተመለከተ፤

39. አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚያድጉበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ ኤጀንሲው የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር ከማድረጉ በፊት በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፣ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸውን ለይቶ መረጃውን ሊይዝና በዚህም መሰረት በየአመቱ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራዝነት የሚሸጋገሩትን መጠን በማቀድ ተግባራዊ መደረግ አለበት፤ የሽግግሩን ዕቅድ በተመለከተም በየደረጃው ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ለተግባራዊነቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸውና ተገቢውን ድርሻ እንዲወጡ መደረግ አለበት፤

40. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉት ኢንተርፕራይዞች በየዓመቱ ከ1-2% ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ለመሸጋገር ግብ የጣለ ቢሆንም በየደረጃው ያሉት ኢንተርፕራይዞች የእያንዳንዱ ብዛት ስንት እንደነበረ በግቡ ላይ በቁጥር ባለመጠቀሱ ዕቅዱ መሳካቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ከተከለሱ ዶክመንቶች በተገኝ መረጃ መሰረት ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃዎች ለማሸጋገር የማሸጋገሪያ ስትራቴጂውን ያለመረዳትና የተረዱትንም ስራ ላይ ለመዋል እንደተቸገሩ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

41. ኢንተርፕራይዞቹ በማዕከላቱ ውስጥ ከአምስት አመት በላይ መቆየት እንደሌለባቸው ውል ሊገቡ እና በውሉ መሰረት ተፈጻሚ መሆኑ ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ኢንተርፕራያዞቹ በማዕከላቱ በሚቆዩበት የቆይታ ጊዜ መክፈል የሚገባቸው የኪራይ ተመን በየክልል በማውጣት በየወሩ እየከፈሉ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

42. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

43. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በየአመቱ በማምረቻ መሸጫ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያው ላይ ስልጠና መሰጠቱ፣ በአብዛኛው ክልሎች የመሸጫ እና የማምረጫ ክላስተር ማዕከላት መመሪያ መሰረት እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የኪራይ ዋጋ እንዲወጣ በማድረግ ቀደም ሲል የገቡ ነባር ኢንተርፕራይዞች ኪራይ እንዲከፍሉ የተደረገ ሲሆን ይህንንም በተለያየ ክትትል እና ድጋፍ ወቅት ለማየት መቻሉ፣
- ከ2003 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ማኑፋክቸሪንግ 2639፣ ኮንስትራክሽን 2056፣ ከተማ ግብርና1589፣ አገልግሎት 2010፣ ንግድ 2373 በድምሩ 10677 ኢንተርፕራይዞች ወደ ታዳጊ መካከለኛ  የተሸጋገሩ መሆኑ፣ ክልሎችም ከመመሪያ ውጭ የተያዙ ሼዶችን የማስለቀቅ ስራ የእቅዳቸው አካል በማድረግ በ2010 በጀት አመት 1593 ሼዶችን ፣2011 በጀት ዓመት እስከ 1ኛው ሩብ አመት 152 ሼዶች በማስለቀቅ ለሌሎች ተጠቃሚዎች የማስተላለፍ ስራ የተሰራ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

## ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ፣

44. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ መስኮች መስፈርት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መዘጋጀት አለበት፡፡ ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቱ መሰረት እየተመረጡ ወደየማዕከላቱ እንዲገቡ መደረግ አለበት፡፡

45. በቀድሞ ኦዲቱ ወቅት  በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የሚገኙ 627 ሼዶች በህገ ወጥ መንገድ ለሶስተኛ ወገን የተከራዩ መሆኑ በተጨማሪም በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት የተዘጋጀውን መመልመያ መስፈርቶች ባልተከተለ መልኩ ወደ ማዕከላቱ የገቡ ግለሰቦችና ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፣ ወደ ማምረቻ ሕንፃ የሚገቡ የኢንተርፕራይዞቹ እንደ የሥራ ባህሪያቸው ሳይለዩ ወደ ህንጻው የገቡ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞቹ በስራቸው ላይ ተጽኖ እንዳሳደረባቸውና በአንዳንድ ህንጻዎችም ላይ ጉዳት እንደደረሰባቸው በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

46. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እና መስፈርቱ ያልተጣሰ ስለመሆኑም ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል የሚደረግበት አሠራር መዘርጋት እንዳለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

47. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

48. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በየአመቱ በማምረቻና መሸጫ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያው ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤
- በአብዛኛው ከተማ አስተዳደሮች በክላስተር ማዕከላት በመመሪያው መሰረት እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የኪራይ ዋጋ እንዲወጣ መደረጉ፤
- ቀደም ሲል የገቡ ነባር ኢንተርፕራዞች ኪራይ እንዲከፍሉ መደረጉ፤
- ለዚህም የተለያየ ክትትልና ድጋፍ መደረጉ፤
- በየክልሉ የቆይታ ጊዜያቸውን የጨረሱና ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች መረጃ እንዲለይና የማደራጀት ስራ እንዲሰራ ክትትልና ድጋፍ መደረጉ፤
- በቀሪ የትግበራ ወቅት ክትትልና ድጋፍን በማጠናከር ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እቅድ መያዙ፣

ታውቋል፡፡

## የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት በተመለከተ፤

49. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች የሚመጋገቡ፣ የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥር የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ በፌዴራሉም ሆነ በክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲዎች ይህ ትስስር መፈጠሩ መረጋገጥ አለበት፤

50. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ወደ ማዕከላት በሚገቡ ኢንተርፕራይዞቹ መካከል የፊትና የኋላ የገበያ ትስስር አለመፈጠሩን፣ ወደ ማምረቻ ሕንፃ ወይም ሼድ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞቹ የሚያመርቱትን ምርት የመሸጫና የማሳያ ቦታ እንደ ማይመቻችላቸው በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

51. ወደ ማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸው የሚመጋገቡ፣ የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥሩ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸው ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት እንዲያድጉ ተገቢው ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

52. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

53. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በኦሮሚያ፤ በትግራይ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች፤ በአማራ እና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ  እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ከህዳር 25 እስከ ታህሳስ 09/2010 የዝግጅትና የተግባር ምዕራፍ ሥራዎች ድጋፍና ክትትል ስራ ሪፖርት ላይ በአማራ ክልል በታዩ ከተሞች ለወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለይ አዲስ ለተደረጁ አንቀሳቃሾች ያለምንም ጨረታ በቀጥታ የገበያ ትስስር የሚደረግበት መመሪያ መዘጋጀቱ፤
- ከተሞችም ይህንን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ በኮንስትራክሽን ዘርፍ አዲስ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ሰፊ የገበያ ትስስር መፈጠሩ፤
- በድሬደዋ ከተማ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታታት የወጣው የገበያ ልማትና ግብይት መመሪያ ተግባር ላይ አለማዋሉ፤ በተለይ የጨረታ ሰነድ በነፃ ለጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲሰጥ የተቀመጠ ቢሆንም በኤጀንሲ ከሚወጡት ጨረታዎች በስተቀር ሌሎች ተቋማት የጨረታ ሰነድ በሽያጭ ስለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ቅሬታ እያቀረቡ መሆናቸው፤
- ኢንተርፕራይዞች  የገበያ ትስስር ከተፈጠረላቸው በኋላ በአቅርቦት፤በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ ሆኖ ካለመገኘታቸው ጋር ተያይዞ ሆስፒታሎችና ከዩኒቨርስቲዎች ጋር ያለው የገበያ ትስስር እየተዳከመ መምጣቱ፤

- ኢግዚቢሽንና ባዛሮች ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የገበያ እድሎችን ለይቶ በመንግስት ተቋማት በዩኒቨርስቲዎች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ከመፍጠር አንጻር በደቡብብሔር ብሔየረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሰፊ ክፍተት መኖሩ፤
- በተለያዩ ዘርፎች የገበያ እድሎችን በጥናት በመለየት ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙበት ለማድረግ እጥረት መኖሩ፤
- በኦሮሚያ፣ በትግራይ፤ በደቡብ ብሔር ብሔየረሰቦችና ሕዝቦች፣ በአማራ፣ በሀረሪ ክልሎች እና በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የአካባቢ የገበያ አማራጮች እንዲጠቀሙ ከልየታ ጀምሮ እየተሰራ ያለው ስራ በቂ አለመሆን፤
- ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያላቸውን ፕሮጀክት አሳውቀው ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ትሥሥር እንዲውል ከማድረግ አኳያ ፈቃደኝነት አለማሳየታቸው፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የማምረቻ፣መሸጫና የገበያ ማዕከላት መጠቀሚያ የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ፤

54. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት የዋጋ ተመን በክልል ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮዎች ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅ በማድረግ በጸደቀው ተመን መሰረት ኢንተርፕራይዞቹ የአገልግሎት ክፍያውን እንዲከፍሉ መደረግ አለበት፡፡

55. በኦዲቱ ወቅት ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ተመን ወጥነት ባለው መልኩ በየክልሎቹ ተመኑ ያልተዘጋጀ እና እና ክፍያውም በተሟላ ሁኔታ እንደማይሰበሰብ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

56. ኢንተርፕራያዞቹ በማዕከላቱ በሚቆዩበት የቆይታ ጊዜ መክፈል የሚገባቸው የኪራይ ተመን በየክልል በማውጣት በየወሩ እየከፈሉ መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

57. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

58. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- መደበኛ የብድር ክትትል ፕሮግራም በማውጣት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሞያ የብድር ክትትል የማድረግ ስራ የሚሰሩ መሆኑ፣
- የብድርና ቁጠባ ተቋማትም የብድር መከታተያ ፎርማት በማዘጋጀት ኢንተርፕራይዞችን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑ፣ የታየ የተሻሻለ ተግባር ሲሆን፤
- ከማምረቻና መሸጫ ማዕከላት መመሪያ አተገባበር ጋር ተያይዞ የኪራይ መጠን ለኢንተርፕራይዞች በማዕከሉ ውስጥ ቆይታ የሚወሰን ሲሆን በመጀመሪያ አመት 25% በሁለተኛው አመት 50% በሶስተኛው አመት 75% እና በአራተኛው እና በአምስተኛው አመት ሙሉ የክራይ ዋጋ ይከፍላሉ በሚል ቢቀመጥም ይህንን የክራይ አከፋፈል ተከትሎ ተግባራዊ አለማድረግ፣
- በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት የከተማው ገቢዎች ፅ/ቤት ገቢ የመሰብሰብ ስራ ቢሰራም መሰብሰብ ያለበት ኪራይ ሁሉም በአግባቡ መሰብሰቡን በተመለከተ በቂ ክትትልና ድጋፍ አለመደረጉ፤
- ለሚዘጋጁ ሼዶችና የገበያ ማዕከላት የአካባቢውን የገበያ ዋጋ መሰረት ያደረገ የክራይ ዋጋ ያልተተመነ መሆኑ፤
- ወርሃዊ የኪራይ መጠኑ ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ያነሰ መሆኑ፤ እንዲሁም በየዓመቱ የሚከፈለው የክራይ መጠን በመመሪያው መሰረት በመጀመሪያው ዓመት 25% በ2ኛ ው ዓመት 50% በሶስተኛው ዓመት 75% በ4ኛው እና በ5ኛው ዓመት የተተመነውን የክራይ ዋጋ ሙሉውን እንዲከፍሉ እና ከ5 ዓመት በኋላ ለሌሎች እንዲያስተላልፉ የሚደረገው ድጋፍ ክትትል ቀጣይነት የሌለው በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ከመጀመሪያው እስከ 5ኛው የክፍያ ልዩነት ተግባራው እየተደረገ አለመሆኑ፣

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል

**ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜን በተመለከተ፤**

59. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ ከ5 ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡ ኢንተርፕራይዞቹም ስለማዕከላቱ አጠቃቀም ውል መግባት ያለባቸው እና ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ከማዕከላቱ እንዲወጡ መደረግ አለበት የኢንተርፕራዞቹ ቆይታ በውሉ መሠረት ተፈፃሚ ስለ መሆኑ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ክትትል መደረግ አለበት፡፡

60. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ኢንተርፕራይዞች በማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ 5 ዓመት እንደሆነ መመሪያው ቢያዝም ከ5 ዓመት በላይ በማዕከላቱ ያስቆጠሩ ኢንተርፕራይዞች እንዳሉ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

61. ኢንተርፕራይዞቹ በማዕከላቱ ውስጥ ከአምስት አመት በላይ መቆየት እንደሌለባቸው ውል ሊገቡ እና በውሉ መሰረት ተፈጻሚ መሆኑ ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

62. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

63. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በየዓመቱ በማምረቻና መሸጫ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያው ላይ ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፤
- ክልሎች ከሥራ ውጪ የተያዙ ሼዶችን የማስለቀቅ ሥራ የእቅዳቸው አካል በማድረግ በ2010 ዓ.ም 1593 ፤በ2011 ዓ.ም ሩብ ዓመት 152 በማስለቀቅ ለሌሎች ተጠቃሚዎች የማስተላላፍ ሥራ የተጀመረ መሆኑ፣
- በአማራ፣ ሀረሬ፣ አፋር ክልሎች እና በድሬደዋ ከአሰራር ውጭ የተያዙ የመስሪያና የመሸጫ ሼዶችና ማዕከላት ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች አለመኖራቸው፤ እንዲሁም እርምጃ የተወሰደባቸው ቢኖሩም በሪፖርት ተካተው እንዲታወቁ አለማድረግ፤

- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ 5 አመት ሆኖ በሚገቡት ውል መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ቢቀመጥም በሁሉም ክልሎች በተሟላ መልኩ ወደ ተግባር አለመግባቱ፤
- ለተከታታይ 5 አመታት የማምረቻና የመሸጫ ማዕከል ተሰጥቷቸው የመመረቂያ መመዘኛ መስፈርት ማሟላት ባለመቻላቸው ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ያልተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት በቀጣይ አይሰጣቸውም ነገር ግን ሌሎች ድጋፎችን እስከ ቀጣይ 2 ዓመት ሊሰጣቸው ይችላል በሚል በመመሪያው ላይ ቢቀመጥም ይህንን ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- በመስሪያና መሸጫ ክላስተር ማዕከላት ላይ ባለ የአፈፃፀም ችግር ምክንያት ነባር ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩም ያልተሸጋገሩም የተሰጣቸውን የማምረቻና የመሸጫ ማዕከል እንደ ርስት በመቁጠር ቦታውን ለመልቀቅ ፍቃደኛ አለመሆን፤
- አመራሩም በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት ስራዎችን መምራት ባለመቻሉ ወደ ስራ ለሚገቡ አዲስ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታ እጥረት እያጋጠመ ከመሆኑ በተጨማሪ በስራ ፈላጊዎችና በተገልጋዮች የፍትሃዊነት ጥያቄ መነሳቱ፤
- በከተሞች የሚገኙ የከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ (ቢሮዎች) የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ድጋፍ አቅርቦት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞች አቅም እያደገና የስራ ስፋት እየጨመረ ሲሄድ በመገምገም ተጨማሪ የስራ እድል እንዲፈጥሩና ስራቸውን እንዲያስፋፉ በሚል የኢንተርፕራይዙን የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ተለዋጭ የመስሪያ ወይም የመሸጫ ቦታ እንዲሰጥ አለመደረጉ፤

በክትትል ኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከሠጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ድጋፍ በተመለከተ ፤

64. የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ውስጥ ተደራጅተው የገቡ ኢንተርፕራይዞች ከማዕከላቱ የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ሄደው የሚገቡበት በኢንዱስትሪ ዞኖች እንደ ሥራው ባህሪያቸው ለኢንተርፕራዞቹ አስቀድሞ ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡

65. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ የቆይታ ጊዜቸውን ጨርሰው የሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ከተመረቁ በኃላ ምንም ዓይነት ድጋፍ እንደማይደረግላቸውና ግማሾቹም ከማዕከላቱ ያልወጡ መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

66. ከማዕከላቱ የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ወደመካከለኛ ኢንተፕራይዝነት ለሚሸጋገሩ ተቋማት በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥም ሆነ በሌላ አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች ለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ እንደ ሥራው ባህሪያቸው በመመሪያው መሰረት አስቀድሞ ቦታ ሊዘጋጅላቸው እና ተገቢው የፋይናንስ አቅርቦት የሚያገኙበት መንገድ ሊዘጋጅላቸው እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

67. ኤጀንሲው ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

68. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በየአመቱ በማምረቻ መሸጫ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያው ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤
- በአብዛኛው ክልሎች የመሸጫ እና የማምረቻ ክላስተር ማዕከላት መመሪያ መሰረት እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የኪራይ ዋጋ እንዲወጣ በማድረግ ቀደም ሲል የገቡ ነባር ኢንተርፕራይዞች ኪራይ እንዲከፍሉ የተደረገ ሲሆን ይህንንም በተለያየ ክትትል እና ድጋፍ ወቅት ለማየት መቻሉ፤
- ከ2003 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ማኑፋክቸሪንግ 2639፤ ኮንስትራክሽን 2056፤ ከተማ ግብርና1589፤ አገልግሎት2010፤ ንግድ 2373 በድምሩ 10677 ኢንተርፕራይዞች ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ መሆኑ

በክትትል ኦዲቱ የታየ የተሻሻለ ተግባር ነው፡፡(ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተያይዟል)

## ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ፤

69. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ

ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ሊያቅዱና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

70. በቀድሞ ኦዲቱ ወቅት  የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፣ በኦሮሚያ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በናሙና ከታዮት የፋይናንስ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ኤጀንሲው ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ወጥነት በለው መልኩ የማይከነወን መሆኑን፣ በተለይም ብድር የማስመለስ ሂደት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን እና በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚመለከታቸው ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም አተገባበር ላይ ወጥነት ባለው መልኩ አለመከናወኑን አለመዳበሩን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

71. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና  የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ለያዕቅዱና በዕቅዱም መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህንንም ለመተግበር ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ ይገባል፡፡

72. ኤጀንሲው በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተልኳል፡፡

73. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- በሙሉ ያገጠሙ ችግሮች ከመፈታት አንጻር በተዋረድ ባለዉ መዋቅር ችግር እያጋጠመ ቢሆንም በፌዴራል ደረጃ ባሉ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ጭምር ችግሩን ለመፍታት ጥረት የተደረገ መሆኑ፣
- ከስራ አማራጮች ጋር ተያይዞ ንግድ ፍቃድ በጥቃቅንና አነስተኛ የሚሰማሩ ተብሎ ከንግድ ቢሮዎች ተሰርቶ የተሰጠዉ ከፌዴራል ንግድ ሚንስቴር ጋር በመቀናጀት ችግሩን እንዲፈታ በወረደዉ ሰርኩላር በሁሉም አካባቢ ችግሩን መፍታት መቻሉ፤
- ከንግድ ስም ስያሜ ጋር ተያይዞ በፌዴራል ደረጃ በንግድ ሚኒስቴር ብቻ ሲሰጥ የነበረ ችግር በዚሁ ቴክኒክ ኮሚቴ ጭምር ወደ ሁሉም ክልሎች ወርዶ አገልግሎት በከተማ ደረጃ እየተሰጠ መሆኑ፣

- ከመስሪያ ቦታ ጋር ተያይዞ በመኖሪያ ቤት መስራት የማይቻል የነበረ ሲሆን ይህም እንዲፈታ ተደርጎ ተግባር ላይ መዋሉ፣
- ከብቃት ማረጋገጫ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በሁሉም ተቋማት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ለእንግልት ምልልስ ከመዳረጉ በዘለለ ፍቃዱንም የሚሰጥ ስላልነበረ ይህም አብዛኛዉ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጡ ተቋማት እንዲተዉ መደረጉ፣
- በጥሪት ማፍሪያ ላይ የተሰማሩ ዜጎች በስትራቴጂው መሰረት ንግድ ፍቃድ ሳያወጡ በምዝገባ ብቻ ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉ፣
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (የቲን ነምበር) በዞን ከተማ ብቻ ሲሰጥ የነበረዉ ወደታች እንዲወርድ መደረጉ፣
- ከዉልና ማስረጃ አገልግሎት ጋር ያለዉ ለክልሎች ቢወርድም አሁንም ማነቆ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

74. በቀድሞው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸምን በተመለከተ በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶች እና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ ለአሁኑ የፌዴራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን የሚመለከቱ ግኝቶች እና የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው፤

- የብድር አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ እንዲቻል ከመደበኛ ብድር በተጨማሪ ሌሎች አማራጮችን መከተል አስፈላጊ መሆኑን ታምኖበት አስፈላጊው ጥናት እንዲጠና ተደርጎ በጥናቱ ግኝት ላይ ተመስርቶ በ2009 ዓ/ም የ10 ቢሊየን ብር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ እንዲመደብ መደረጉ፤
- ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ዘመናዊ የአሰራር ስርዓትን ለመዘርጋት የኮር ባንኪንግ ሲስተምን ለመጠቀም የተጀመረ ሥራ መኖሩ ፤
- በፌዴራል ደረጃ የቁጠባና የፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ በማዋቀር በብሄራዊ ባንክ ሰብሳቢነት ኤጀንሲው በጸሀፊነት እንዲሁም አነስተኛ ማይክሮ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም ማህበር ፤ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአባልነት የሚሳተፉበት ቴክኒክ ኮሚቴ የጋራ አቅድ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ መሆኑ በክልል ደረጃ 3ቱም ፈጻሚ አካላት ማለትም የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ፤የአነስተና ብድር አቅራቢ ተቋማትና የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ በማዋቀር በተቀናጀ መልኩ የድጋፍና ክትትል ስራ መሰራቱ፤ለክልሎች መሰረተ ልማት ችግር ያለባቸዉን ሼዶች በመለየት በተላከዉ የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት እንዲልኩ በማድረግ መረጃዉን አደራጅቶ ለዉሀና መስኖ ኢነርጂ ሚኒስቴር ደብዳቤ በመጻፍ ችግሩ እንዲፈታላቸዉ ጥረት መደረጉ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤት በኩል ለአንዳንድ ክልሎች በዲስትሪክታቸው አማካኝነት ችግሮች እንዲፈቱላቸዉ ደብዳቤ ተጽፎ ክትትል እየተደረገ መገኘቱ በሚደረጉ ሱፐርቪዥኖችም ችግሮችን በመለየት በክልሉ የበላይ አመራሮች እንዲፈታ ግብረ መልስ መሰጠቱ፤
- ለስራ እድል ፈጠራ እና ለኢንተርፕራይዞች ልማት በሚውሉ የመስሪና የመሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ መስጠት የሚያስችል ጥናት በ2010 ዓ.ም. በኤጀንሰው በኩል መጠናቱ፤ በአምስቱ የእድገት ተኮር ዘርፎች ላይ በሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች የሚታዩ ችግሮችን ለመለየት በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ችግርን በሚመለከት የጥናት ሰነዱን መነሻ በማድረግ ከክልሉ የዘርፍ አመራሮች ጋር በታዩ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ የምክክር መድረክ የተዘጋጀ መሆኑ፤
- ክልሎች በእቅዳቸው ውስጥ የሼድ ግንባታ እንዲያካትቱ በማድረግ አስፈላጊው በጀት ተመድቦ ግንባታው እንዲካሄድ የድጋፍ ክትትል ስራው እየተሰራ መሆኑ
- በሁለተኛው ጂቲፒው በ5 ዓመት 15000 ሼዶችን ለመገንባት ታቅዶ በ3 ዓመት ወስጥ 19090 (127%) መገንባት መቻሉ፤
- በየአመቱ በማምረቻ መሸጫ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያው ላይ ስልጠና መሰጠቱ፤ በአብዛኛው ክልሎች የመሸጫ እና የማምረቻ ክላስተር ማዕከላት መመሪያ መሰረት እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የኪራይ ዋጋ እንዲወጣ በማድረግ ቀደም ሲል የገቡ ነባር ኢንተርፕራይዞች ኪራይ አንዲከፍሉ የተደረገ ሲሆን ይህንንም በተለያየ ክትትል እና ድጋፍ ወቅት ለማየት መቻሉ፤
- ከ2003 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ማኑፋክቸሪንግ 2639፤ ኮንስትራክሽን 2056፤ ከተማ ግብርና1589፤ አገልግሎት2010፤ ንግድ2373 በድምሩ 10677 ኢንተርፕራይዞች ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ መሆኑ
- በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤ በደቡብ፤ በአማራ እና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ከህዳር 25 እስከ ታህሳስ 09/2010 የዝግጅትና የተግባር ምዕራፍ ሥራዎች ድጋፍና ክትትል ስራ ሪፖርት ላይ በአማራ ክልል በታዩ ከተሞች ለወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለይ አዲስ ለተደረጁ አንቀሳቃሾች ያለምንም ጨረታ በቀጥታ የገበያ ትስስር የሚደረግበት መመሪያ መዘጋጀቱ፤

- ከተሞችም ይህንን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ በኮንስትራክሽን ዘርፍ አዲስ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ሰፊ የገበያ ትስስር መፈጠሩ፤
- መደበኛ የብድር ክትትል ፕሮግራም በማውጣት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሞያ የብድር ክትትል የማድረግ ስራ የሚሰሩ መሆኑ እና የብድርና ቁጠባ ተቋማትም ብድርም መከታተያ ፎርማት በማዘጋጀት ኢንተርፕራይዞችን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑ፤
- በየዓመቱ በማምረቻና መሸጫ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያው ላይ ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፤ ክልሎች ከሥራ ውጪ የተያዙ ሼዶችን የማስለቀቅ ሥራ የእቅዳቸው አካል በማድረግ በ2010 ዓ.ም 1593፤ በ2011 ዓ.ም ሩብዓመት 152 በማስለቀቅ ለሌሎች ተጠቃሚዎች የማስተላላፍ ሥራ የተጀመረ መሆኑ፤
- ሙሉ በሙሉ ያገጠሙ ችግሮች ከመፈታት አንጻር በተዋረድ ባለዉ መዋቅር ችግር እያጋጠመ ቢሆንም በፌዴራል ደረጃ ባሉ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ጭምር ችግሩን ለመፍታት ጥረት የተደረገ ሲሆን በዚህም ቀደም ሲል ከስራ አማራጮች ጋር ተያይዞ ንግድ ፍቃድ በጥቃቅንና አነስተኛ የሚሰማሩ ተብሎ ከንግድ ቢሮዎች ተሰርቶ የተሰጠው ከፌዴራል ንግድ ሚንስቴር ጋር በመቀናጀት ችግሩን እንዲፈታ በወረደዉ ሰርኩላር በሁሉም አካባቢ ችግሩን መፍታት መቻሉ፤
- የንግድ ስም ስያሜ ጋር ተያይዞ በፌዴራል ደረጃ በንግድ ሚኒስቴር ብቻ ሲሰጥ የነበረ ችግር በዚሁ ቴክኒክ ኮሚቴ ጭምር ወደ ሁሉም ክልሎች ወርዶ አገልግሎት በከተማ ደረጃ እየተሰጠ መሆኑ፣
- ከመስሪያ ቦታ ጋር ተያይዞ በመኖሪያ ቤት መስራት የማይቻል የነበረ ሲሆን ይህም እንዲፈታ ተደርጎ ተግባር ላይ መዋሉ፣
- ከብቃት ማረጋገጫ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በሁሉም ተቋማት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ለእንግልት ምልልስ ከመዳረጉ በዘለለ ፍቃዱንም የሚሰጥ ስላልነበረ ይህም አብዛኛው ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጡ ተቋማት እንዲተው መደረጉ፣
- በጥሪት ማፍሪያ ላይ የተሰማሩ ዜጎች በስትራቴጂ መሰረት ንግድ ፍቃድ ሳያወጡ በምዝገባ ብቻ ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉ፣
- የቲን ነበር በዞን ከተማ ብቻ ሲሰጥ የነበረዉ ወደታች እንዲወርድ መደረጉ ከተሰሩ ስራዎች ዉስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ከዉልና ማስረጃ አገልግሎት ጋር ያለዉ

ለክልሎች ቢወርድም አሁንም ማነቆ መሆኑ እንደክፍተት የሚታይና እየተሰራ ያለበት መሆኑ ታውቋል፡፡

## 3.2፤ እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፤

- በየክልሎች የወጣቶች ተዘዋሪ ብድር ፈንድ በከተሞችና በገጠር ላሉ ለይቶ በመመደብና የተሰራጨውንም ብድር አፈፃፀም በገጠርና በከተማ ለይቶ ከማቅረብ አንፃር በትግራይ፤ በሀረሪ፤ በኦሮሚያና፤ በአማራ ክልል ችግር ያለ መሆኑ
- በፌዴራል ደረጃ ሞዴል የአሰራር መመሪያ በ2005 ዓ/ም በማዘጋጀት ለክልሎች ማውረድ የተቻለ ሲሆን ክልሎችም እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመቃኘት በክልላቸው/ ከተማ አስተዳደራቸው ካቢኔ በማፀደቅ በስራ መመሪያነት እየተጠቀሙ የሚገኙ ያሉ ሲሆን በአንፃሩ ከመነሻው አሰራሩን ዘርግተው ወደ ስራ ያልገቡ ክልሎች መኖራቸው
- አሰራሩን ዘርግተው አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት ክልሎች በሂደት ያቋረጡ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገለጽ የአሰራር ክፍተት ስለነበር ቤሄራዊ ባንክ በውጭ አማካሪዎች በማስጠናት የመጀመሪያ ረቂቅ ቀርቦ አስተያየት ተሰጥቶበት መዳበር የቻለ ቢሆንም መመሪያውን አጽድቆ ወደ ክልሎች /ከተማ አስተዳደሮች የማሰራጨት ተግባር እስካሁን መፈፀም አለመቻሉ፤
- በአምስቱ የዕድገት ዘርፎች ላይ ያሉ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት እንደታየው በአዳማ ከተማ አስ/የ01 ቀበሌ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢየ ለስራ ምቹ ባልሆኑ ቦታዎች የተገነቡና መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው ሼዶችና ክለስተሮች ያለስራ መቀመጣቸው፤
- ለአገልግሎት ዘርፍ የተሰሩት ሼዶችና ክላስተሮች አገልግሎት ለመስጠት ሽንት ቤት ስለሌላቸው በጤና ፅ/ቤት እየታሸጉ ኢንተርፕራይዞች መጉላላታቸው፤
- በዱከም ከተማ አስተዳደር የ01 ቀበሌ የአ/ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ መሰረተ ልማት ያልተሟሟላላቸው መሆኑ ፤
- በአሰላ ከተማ አስተዳደር የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፅ/ቤት የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ያልተጣጣመ መሆኑ፤

- በሻሸመኔ ከተማ የተገነቡትና በመገንባት ላይ ያሉትም ለስራ ምቹ ያልሆኑና የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው በመሆን፣ 64 ሼዶች በመሰረተ ልማት ችግር ወደስራ ያልገቡ መሆኑ፣
- የስራ እድል ፈጠራና ለኢንርፕራይዞች ልማት በሚውሉ የመስሪያና መሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ጥናት ሰነድ ላይ፣ በ2005 የፀደቀው አደጋን የሚቋቋም አረንጓዴና ተደራሽ የከተሞች ልማት ፖሊሲ ላይ እንደተገለፀው በቂ መሰረተ ልማት አቅርቦት ያለው መሬት በማዘጋጀትና ከዚህ ውስጥ ቅድሚያ ለጥቃቅንና አነስተና ተቋማት ማምረቻ ቦታ በመለየት በተመጣጣኝ ዋጋ ለተቋማቱ ማከራየት ቢሆንም በጥናቱ በቀረበ ቃለ መጠይቅ የተሰጠ መልስ እንደሚያመለክተው በመብራት ችግር ወደ ስራ ያልገቡ የማምረቻ ሼዶች በተለያዩ ከተሞች በመኖራቸው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቅድሚያ ለመስጠት እንዲችል በመብራት ኃይል የጋራ እቅድ በማዘጋጀት እና በጋራ ለመገምገም መግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣
- በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብና፣ በአማራ፣ በሀረሪ፣ በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ከህዳር 18-29/2011 ድረስ የተካሄደ የ100 ቀናት ትግበራ እና የ2011 በጀት አመት ስራዎች አፈፃፀም ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ከመስሪያ ቦታ ድጋፍ ጋር በተያያዘ ትልቁ ማነቆ የመሰረተ ልማት ችግር ሲሆን በታዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የችግሩ ስፋት ቢለያይም በአብዛኞች የተላለፉ ሼዶች የታዩ የመብራት፣ የውሃ፣ የመፀዳጃ ቤት ያለመሟላት ችግር መኖሩ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለይም መብራት ባለመሟላቱ እና በትራንስፎርመር ችግር የተጠናቀቁ ሼዶች ለኢንተርፕራይዝ ለማስተላለፍ አለመቻሉ፣
- በመሰረተ ልማት ችግር ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ህንፃዎችና ሼዶች በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለመፍታት በማሰብ የተሰበሰበ መረጃ ላይ እንደሚያመለክተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ በ2008/2009/2010 ዓ.ም ለቆጣሪ፣ መስመር ዝርጋታ እና ለትራንስፎርመር ማስገቢያ ጠቅላላ 35.304.340.07 ብር ለኢትዮጵያ ለኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተከፈለ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስተጠናቀቀ ድረስ የተገነቡት ህንፃዎችና ሼዶች የኤሌትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣

- በድሬደዋ ከተማ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታታት የወጣው የገበያ ልማትና ግብይት መመሪያ ተግባር ላይ አለማዋሉ፤
- በተለይ የጨረታ ሰነድ በነፃ ለጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲሰጥ የተቀመጠ ቢሆንም በኤጀንሲ ከሚወጡት ጨረታዎች በስተቀር ሌሎች ተቋማት የጨረታ ሰነድ በሽያጭ ስለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ቅሬታ እያቀረቡ መሆናቸው፤
- ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ከተፈጠረላቸው በኋላ በአቅርቦት፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ ሆኖ ካለመገኘታቸው ጋር ተያይዞ ሆስፒታሎችና ከዩኒቨርስቲዎች ጋር ያለው የገበያ ትስስር እየተዳከመ መምጣቱ፤
- ኢግዚቢሽንና ባዛሮች ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የገበያ እድሎችን ለይቶ በመንግስት ተቋማት በዩኒቨርስቲዎች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ከመፍጠር አንጻር በደቡብ ክልል ሰፊ ክፍተት መኖሩ፤
- በተለያዩ ዘርፎች የገበያ እድሎችን በጥናት በመለየት ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙበት ለማድረግ እጥረት መኖሩ፤
- በኦሮሚያ ፤በትግራይ፤በደቡብና ፤በአማራ ፤በሀረሪ ፤በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የመስክ ምልከታ በተካሄደባቸው ከተሞች የአካባቢ የገበያ አማራጮች እንዲጠቀሙ ከልየታ ጀምሮ እየተሰራ ያለው ስራ በቂ አለመሆን፤
- ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያላቸውን ፕሮጀክት አሳውቀው ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ትሥሥር እንዲውል ለማድረግ ፈቃደኝነት አለማሳየታቸው፤
- ከማምረቻና መሸጫ ማዕከላት መመሪያ አተገባበር ጋር ተያይዞ የክራይ መጠን ለኢንተርፕራይዞች በማዕከሉ ውስጥ ቆይታ የሚወሰን ሲሆን በመጀመሪያ አመት 25% በሁለተኛው አመት 50% በሶስተኛው አመት 75% እና በአራተኛው እና

በአምስተኛው አመት ሙሉ የክራይ ዋጋ ይከፍላሉ በሚል ቢቀመጥም ይህንን የክራይ አከፋፈል ተከትሎ ተግባራዊ አለመደረጉ ፤

- በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት የከተማው ገቢዎች ፅ/ቤት ገቢ የመሰብሰብ ስራ ቢሰራም መሰብሰብ ያለበት ኪራይ ሁሉም በአግባቡ መሰብሰቡን በተመለከተ በቂ ክትትልና ድጋፍ አለመደረጉ፤
- ለሚዘጋጁ ሼዶችና የገበያ ማዕከላት የአካባቢውን የገበያ ዋጋ መሰረት ያደረገ የክራይ ዋጋ ያለተተመነ መሆኑ፤
- ወርሃዊ የክራይ መጠኑ ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ያነሰ መሆኑ፤
- እንዲሁም በየዓመቱ የሚከፈለው የክራይ መጠን በመመሪያው መሰረት በመጀመሪያው ዓመት 25% በ2ኛ ው ዓመት 50% በሶስተኛው ዓመት 75% በ4ኛው እና በ5ኛው ዓመት የተተመነውን የክራይ ዋጋ ሙሉውን እንዲከፍሉ እና ከ5 ዓመት በኋላ ለሌሎች እንዲያስተላልፉ የሚደረገው ድጋፍ ክትትል ቀጣይነት የሌለው በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ከመጀመሪያው እስከ 5ኛው የክፍያ ልዩነት ተግባራው እየተደረገ አለመሆኑ፤
- የፌዴራል ከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክተር የ2010 ዓ/ም የመጀመሪያ ስድስት ወራት የክልሎች ዕቅድ አፈፃፀም ግብረ መልስ ላይ በአማራ፣ ድሬደዋ፣ ሀረሬ ፣ አፋር ክልሎች ከአሰራር ውጭ የተያዙ የመስሪያና የመሸጫ ሼዶችና ማዕከላት ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች አለመኖራቸው፤
- እንዲሁም እርምጃ የተወሰደባቸው ቢኖሩም በሪፖርት ተካተው እንዲታወቁ አለመደረጉ፤
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ 5 አመት ሆኖ በሚገቡት ውል መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ቢቀመጥም በሁሉም ክልሎች በተሟላ መልኩ ወደ ተግባር አለመገባቱ፤
- ለተከታታይ 5 አመታት የማምረቻና የመሸጫ ማዕከል ተሰጥቷቸው የመመረቂያ መመዘኛ መስፈርት ማሟላት ባለመቻላቸው ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ያልተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት በቀጣይ አይሰጣቸውም ነገር ግን ሌሎች ድጋፎችን እስከ ቀጣይ 2 ዓመት ሊሰጣቸው ይችላል በሚል ቢቀመጥም ይህን ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- ከመስሪያና  መሸጫ ክላስተር ማዕከላት ላይ ባለ አፈፃፀም ችግር ምክንያት ነባር ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩም ያልተሸጋገሩም የተሰጣቸውን የማምረቻና የመሸጫ ማዕከል እንደ ርስት በመቁጠር ቦታውን ለመልቀቅ ፍቃደኛ አለመሆን፤
- አመራሩም በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት ስራዎችን መምራት ባለመቻሉ ወደ ስራ ለሚገቡአዲስ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታ እጥረት እያጋጠመ ከመሆኑ በተጨማሪ በስራ ፈላጊዎችና በተገልጋዮች የፍትሃዊነት ጥያቄ መነሳቱ፤
- በከተሞች የሚገኙ የከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ (ቢሮዎች) የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ድጋፍ አቅርቦት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞች አቅም እያደገና የስራ ስፋት እየጨመረ ሲሄድ በመገምገም ተጨማሪ የስራ እድል እንዲፈጥሩና ስራቸውን እንዲያስፋፉ በሚል የኢንተርፕራይዙን የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ተለዋጭ የመስሪያ ወይም የመሸጫ ቦታ እንዲሰጥ አለመደረጉ፤ ታውቋል፡፡

# ክፍል አራት

## 75. የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የእርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ቀደም ሲል በተዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ አንድ

## የተፈጠሩ ኢንተርፕራይዞች ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች መረጃ፤

## በዘርፍ እና ሽግግር ባደረጉበት አመት የሚያሳይ መረጃ

| የተሰማሩበት ዘርፍ | 2003 | | 2004 | | 2005 | | 2006 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ |
| አገልግሎት | 48343 | 11 | 12243 | 69 | 12681 | 117 | 14460 | 312 |
| ኮንስትራክሽን | 10675 | 68 | 3330 | 61 | 4936 | 143 | 4973 | 313 |
| ንግድ | 91844 | 3 | 17449 | 22 | 18259 | 112 | 22313 | 374 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 21319 | 108 | 3119 | 103 | 3753 | 271 | 4428 | 541 |
| ከተማ ግብርና | 16622 | 7 | 3504 | 61 | 9073 | 143 | 9897 | 107 |
| ድምር | 188803 | 197 | 39645 | 299 | 48705 | 786 | 56061 | 1647 |

| የተሰማሩበት ዘርፍ | 2007 | | 2008 | | 2009 | | 2010 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ | የተፈጠሩ | የተሸጋገሩ |
| አገልግሎት | 15193 | 438 | 3263 | 278 | 10350 | 377 | | |
| ኮንስትራክሽን | 6412 | 388 | 2367 | 390 | 6104 | 326 | | |
| ንግድ | 21775 | 576 | 5296 | 395 | 12745 | 483 | | |
| ማኑፋክቸሪንግ | 6623 | 702 | 1880 | 424 | 5194 | 321 | | |
| ከተማ ግብርና | 13251 | 137 | 1312 | 118 | 11844 | 125 | | |
| ድምር | 63254 | 2241 | 14091 | 1605 | 46237 | 1632 | | |

## አባሪ 2

# የፌዴራል የከተሞችና የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተከለሱ ማስረጃዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የተከለሰው መረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|
| 1 | የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/201 የፌዴራል የከተሞችና የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ | |
| 2 | በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አክሲዮን ማህበር የካ/አ.ማ/ቅ/ፅ/ቤት ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የብድር ተጠቃሚ የሆኑ ማሕበራት ዝርዝር | |
| 3 | በዝርፍ የድጋፍ ማእቀፍ መመሪያዎች ዙሪያ የተሰጠ የስልጠና ሪፖርት (ህዳር 2011 | |
| 4 | የከተሞች የስራ አድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና የ2009ዓ/ም የዝግጅትና የተግባር ምዕራፍ ተግባራት አፈጻጸም ለመከታተልና ለመደገፍ የተደረገ ሱፐርቪዥን የሁሉም ክልሎች ፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ድሬድዋ አስተዳደር ማጠቃለያ ሪፖርት (ጥር 2009) | |
| 5 | ለሁሉም ዳይሬክቶሬቶች የተሰጠ ግብረ መልስ | |
| 6 | የ2009 በጅት አመት የ6 ወር አፈጻጸም መነሻ በማድረግ ለ9ኙ ክልሎችና ለ2ቱ ከትማ አስተዳደሮች የተሰጠ ግብረ መልስ (ጥር 2009 ዓ.ም) | |
| 7 | የኢንተርፕራይዞችን ልማት የሚያደናቅፉ ተግዳሮቶችን ለይቶ እንዲፈቱ ለማድረግ በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ከ13/07-14//07/2011 ዓ.ም በአዳማ ከትማ ከዘርፍ ፈጻሚና ባለድርሻ ተቋማት አመራሮች ጋር የተካሄደ የዉይይት መድረክ አፈጻጸም ሪፖርት(ታህሳስ 2010) | |
| 8 | የገበያ እድሎች፣ በአራቱ የግብይት ትስስር ስርዓቶች ፣ የማስታዎቂያ ዘዴዎች እና የመረጃና ሪፖርት ግኝቶችን አስመልከቶ ለክልልና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የገበያ ልማት የስራ ሂደት መሪዎችና በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚገኙ የገበያ ባለሞያዎች ከጥቅምት 20-27/2010 ዓ.ም የተሰጠ ስልጠና አፈጻጸም ሪፖርት (ህዳር 2010 ዓ. ም) | |
| 9 | በአራቱ የግብይት ስርዓቶች ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶቻቸዉን የማስታወቂያ ዘዴዎች አስመልክቶ በየክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የገበያ ልማት የስራ ሂደት መሪዎችና ባለሞያዎች የተሰጠ የአሰልጣኞች ስልጠና የአፈጻጸም ሪፖርት (ታህሳስ 2011ዓ .ም) | |
| 10 | የስራ እድል ሰጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ በገበያ ጥናት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጅ የፈሳሽ ሳሙና የእሴት ሰንሰለት ጥናት ሰነድ (መጋቢት 2010 ዓ.ም) | |
| 11 | በአራቱ የግብይት ትስስር ስርአቶች ፣ በኢምፓሪየም አጠቃቀም የዉስጥ | |

| | | |
|---|---|---|
| | መመሪያ ፣ ከሸናቾች ሀ/ስ/ማህበር ጋር ያለዉን የገበያ ትስስር እና የመረጃና ሪፖርት ግኝቶችን አስመልክቶ ለክልልና ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የገበያ ልማት የስራ ሂደት መሪዎችና በአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚገኙ የገበያ ባለሞያዎች ስልጠና አፈጻጸም ሪፖርት (ታህሳስ 2009 ዓ.ም) | |
| 12 | በስራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ በገበያ ጥናት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጅ የዶሮ ስጋ ምርት የችሴት ሰንሰለት ጥናት ሰነድ (መጋቢት 2010 ዓ.ም) | |
| 13 | ለስራ እድል ፈጠራና ለኢንተርፕራይዞች ልማት በሚዉሉ የመስሪያና መሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶች ጥናት ሰነድ (ግንቦት 2010 ዓ.ም) | |
| 14 | በኦሮሚያ፣ በትግራይ ፣ በአማራና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬድዋ አስተዳደር ከሚያዚያ 8 እስከ ሚያዚያ 25 ቀን 2010 ዐ.ም ድረስ የ2010 በጀት አመት የ9 ወር ስራዎች ድጋፍና ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት (ግንቦት 2010 ዓ.ም) | |
| 15 | የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ መመሪያን በተመለከተ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ እና ለአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም የተጻፈ ደብዳቤ | |
| 16 | በኦሮሚያ፣ በትግራይ ፣ በደቡብ፣ በአማራና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬድዋ አስተዳደር ከህዳር 25 እስከ ታህሳስ 09 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት እና የተግባር ምዕራፍ ስራዎች ድጋፍና ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት (ታህሳስ 2010 ዓ.ም) | |
| 17 | በመንግስታዊ ድጋፍ አሰጣጥ ላይ የታዩ ችግሮችን እንዲፈቱ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጻፈ ደብዳቤ(ታህሳስ 13/2010 ዓ.ም) | |
| 18 | የተለያዩ ክልሎች የመስክ ምልከታ ሪፖርት ግብረ መልስ(ግንቦት 3/2009 ዓ.ም) | |
| 19 | የከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና የ2009ዓ.ም የተግባርና የማየቃለያ ዕራፍ ተግባራት አፈጻጸም ለመከታተልና ለመደገፍ የተደረገ ሱፐርቪዥ'ን የስድስት ክልሎች ፣ አዲስ አበባ ከተማ እና ድሬድዋ ከተማ አስተዳደር ማጠቃለያ ሪፖርት(ሰኔ 2009ዓ.ም) | |
| 20 | የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክቶሬት የመጀመሪያ ስድስት ወር የክልሎች እቅድ አፈጻጸም ግብረ መልስ (የካቲት 2010ዓ.ም) | |
| 21 | የ1ኛ ሩብ አመት የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሪፖርት ግብረ መልስ (ጥቅምት 2010ዓ.ም) | |
| 22 | በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአማራና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ክልሎች እና በድሬድዋ አስተዳደር ከህዳር 18 እስከ ህዳር | |

| | | |
|---|---|---|
| | 29/2011ዓ.ም ድረስ የተካሂደ የ100 ቀን ዕቅድ ትግበራና የ2011 በጀት አመት ስራወች አፈጻጸም ድጋፍና ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ( ታህሳስ 2011 ዓ.ም) | |
| 23 | የ2ኛ የእድገት ትራንሰፎረሜሽን የ2 ዓመት ከ9 ወራት አፈጻጸምና የቀሪ አመታት እቅድ | |
| 25 | ከማስፈጸም አቅም ግንባታ ዘርፍ ለሁሉም ዳሬክቶሬቶች የተላከ ግብረ መልስ (13/10/2009ዓ.ም) | |
| 27 | በ2010 በጀት ዓመት ወደ ታዳጊ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ | |
| 28 | ከኢንተርፕራይዞች ልማት ደይሬክቶሬት ለስትራቴጅክ ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የተላከ የ2011 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ አመት ሪፖርት | |
| 29 | የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክቶሬት የ2010 በጀት አመት ዓመታዊ የዉጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ሰኔ 2010 ዓ.ም) | |
| 30 | የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክቶሬት የ2009 በጀት አመት ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ረቂቅ ሪፖርት (ሐምሌ 2009ዓ.ም) | |
| 31 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ፣ የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2010 በጀት ዓመት የጋራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ሐምሌ 2010 ዓ.ም) | |
| 32 | በፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ካዉንስል ፣ የፋይናንስ ድጋፍ ስትሪንግ ኮሚቴ የ2009 በጀት አመት የ9 ወራት የጋራ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ግንቦት 2009 ዓ.ም) | |
| 33 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ፣ የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የጋራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ጥቅምት 2011 ዓ.ም) | |
| 34 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ፣ የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2011 በጀት ዓመት የጋራ ዕቅድ (ጥቅምት 2011 ዓ.ም) | |
| 35 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ፣ የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2010 በጀት ዓመት የ9ኝ ወራት የጋራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ሚያዚያ 2010 ዓ.ም) | |
| 36 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ፣ የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2010 በጀት ዓመት የ6 ወራት የጋራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ጥር 2010 ዓ.ም) | |
| 37 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ፣ የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2010 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የጋራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ጥቅምት 2010 ዓ.ም) | |

| | | |
|---|---|---|
| 38 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት የቁጠባና ፋይናንስ አቅርቦት ቴክኒክ ኮሚቴ የ2010 በጀት ዓመት የተከለሰ የጋራ ዕቅድ (መስከረም 2010 ዓ.ም) | |
| 39 | በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት በ4ኛ መደበኛ ስብሰባ የተቀመጡ ዋና ዋና ዉሳኔዎችና አቅጣጫዎች(መስከረም 2010ዓ.ም) | |
| 40 | ለኢትዮጲያ ልማት ባንክ የማምረቻ መሳሪያ የሚቀርብላቸዉ ኢንዱስትሪዎችን ስለማሳወቅ የታተጻፈ ደብዳቤ (መስከረም/8/2010ዓ.ም) | |
| 41 | በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት የጥናት ዉጤቶች ላይ የተካሄደ የሚዲያ ፎረም ዉይይት ሪፖርት (ህዳር 2011ዓ.ም) | |
| 42 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ማኑዋል(ነሀሴ 2010ዓ.ም) | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 43 | የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር አሰጣጥ መመሪያ ማሻሻያ ስለማድረግ ለማስተባበሪያ ጽፈት ቤት የተጻፈ ደብዳቤ (30/05/2010) | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 44 | የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ የብድር ዋስትና መመሪያ (ሰኔ 2006 ዓ.ም) | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 45 | የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ አሰራር መመሪያ(ጥቅምት 2007ዓ.ም) | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 46 | የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የተሰጠ ብድር መረጃ ማሰባሰቢያ | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 47 | በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ ብድር የወሰዱ ኢንተርፕራይዞች መረጃ | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 48 | በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር አገልግሎት የዉዝፍ መረጃ መሙያ ቅፅ | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 49 | በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር የወሰዱና የአመላለስ ዝርዝር ሁኔታ | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 50 | በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ወስደዉ ዉዝፍ እዳ ያለባቸዉ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 51 | የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ሪፖርት | አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ |
| 52 | ስራ ፈላጊዎች በጥቃቅንና አነስተኛ የሚደራጁበት ዝርዝር የስራ መደቦች ስለማሳወቅ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድ ሚንስቴር የተጻፈ ደብዳቤ(መስከረም 2010ዓ.ም) | |
| 53 | የስራ እድል ፈጠራ እና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ የ2009 በጀት አመት የ6 ወር ዕቅድ አፈጻጸም መነሻ በማድረግ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሰጠ ግብረ መልስ (ጥር 2009ዓ.ም) | |
| 54 | የስራ እድል ፈጠራ ላይ እያጋጠሙ ያሉ ማነቆዎች እንዲፈቱ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ | |

| | | |
|---|---|---|
| | የንግድ ሚንስቴር የተጻፈ ደብዳቤ | |
| 55 | ክፍያ ተከፍሎ መሰረተ ልማት ባለመሟላቱ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ህንጻዎች/ ሼዶች በመለየት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ለመፍታት የተዘጋጀ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ | |
| 56 | የስራ እድል ፈጠራ ላይ እያጋጠሙ ያሉ ማነቆዎች እንዲፈቱ ለፌዴራል ጠቅላይ አቃቢ ህግ የተጻፈ ደብዳቤ(ጥር 2009) | |
| 57 | የ100 ቀናት ዕቅድ ትግበራንና የ2011 በጀት አመት ስራዎች አፈጻጸም ድጋፍና ክትትል ሪፖርት ለክልሎች መላክ (ታህሳስ 17/04/2011) | |
| 58 | የስድስት ወራት ሪፖርት ግብረ መልስ ለሁሉመ ክልሎች መላክ(ጥር 30/05/2011) | |
| 59 | መብራትና ዉሃ አቅርቦት ችግር ያለባቸዉ ሼዶች መፍትሄ እንዲሰጥበት ስለመጠየቅ ለዉሀና መስኖና ኤለክትሪክ ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ (መስከረም /24/2011) | |
| 60 | በድጋሚ የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸዉ ህንጻዎች/ሼዶች መረጃ እንዲላክ ለክልሎች የተጻፈ ደብዳቤ (ጥቅምት 29/2011) | |
| 61 | የ2011 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ አመት አፈጻጸም ላይ የተሰጠ ግብረ መልስ (ህዳር/27/2011) | |
| 62 | በአምስቱ የእድገት ተኮር ዘርፎች ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት (መጋቢት 2010) | |
| 63 | የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ መመሪያን በተመለከተ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፣ ለአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም እንዲሁም ለፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተጻፈ ደብዳቤ(07/06/2010) | |
| 64 | በከተማዉ በመንግስት ድጋፍ አንጻር የሚታዩ ችግሮች ማጣራትን በተመለከተ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የተጻፈ ደብዳቤ (ህዳር 2010) | |
| 65 | በአዲስ አበባ ከተማ ለኢንተርፕራይዞች ከሚደረገዉ የመንግስት ድጋፍ አንጻር በተለያዩ ኤፍ ኤም ሬድዮ ጣቢያዎች ጋር በተደረጉ ቀጥታ የህዝብ ዉይይቶች የተነሱ ችግሮችን በማጣራት የቀረበ ሪፖርት(ታህሳስ 2010) | |
| 66 | የሊዝ ዉልን በተመለክተ የተጻፈ ደብዳቤ | |
| 67 | በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአማራ እና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ አስተዳደር ከሚያዚያ 8-ሚያዚያ 25 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ የ2010 በጀት አመት የ9ወር ስራዎች ድጋፍና ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት (ግንቦት 2010 ዓ.ም) | |
| 68 | በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅና የአሰራር መመሪያዎች ላይ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ባለሞያዎች ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጀ ስልጠና ሪፖርት(መጋቢት 2009 ዓ.ም) | |

| | | |
|---|---|---|
| 69 | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የንግድ ምዝገባና የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት (ህዳር 2010) | |
| 70 | በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት እና በፌ/የከ/ስ/እ/ፈ/ም/ዋ/ኤጀንሲ ቅንጅት በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በተደረገ የመስክ ምልከታ ላይ የተሰጠ ግብረ መልስ(ህዳር 2010) | |
| 71 | በዋልታ ሚዲያና ኮምንኬሽን ተገልጋዮች ፕሮግራም ከዘርፍ ልማት ተገልጋዮች የቀረቦ ቅሬታዎች (መጋቢት 2010) | |
| 72 | ለስራ እድል ፈጠራ እና ለኢንተርፕራይዞች ልማት በሚዉል የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶች ጥናት ሰነድ (ግንቦት 2010) | |
| 73 | የኢንተርፕራይዞችን ልማት የሚያደናቅፍ ተግዳሮቶችን ለይቶ እንዲፈቱ ለማድረግ በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ከ13/07-14/07/2010 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ከዘርፍ ፈጻሚና ባለድርሻ ተቋማት አመራሮች ጋር የተካሄደ የዉይይት መድረክ አፈጻጸም ሪፖርት (ታህሳስ 2010) | |
| 74 | መስሪያና መሸጫ ቦታ አጠቃቀም አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቢሮ ለቀረበዉ ቅሬታ ላይ የተዘጋጀ ሪፖርት (ሚያዚያ 2010) | |
| 75 | በዘርፍ ስትራቴጂ፣ በተሸሻሉ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ስታናዳርዶች ዙሪያ ከየክልሉ ለተዉጣጡ የስራ ሃላፊዎችና ከፍተኛ ባለሞያዎች የተዘጋጀ የአሰልጣኞች ስልጠና ሪፖርት (ሰኔ 26/2010 ዓ.ም) | |
| 76 | ለክልሎች የተላከ የድጋፍ ማእቀፍ መመሪያ(ጥር/2/2010 ዓ.ም) | |
| 77 | የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ግንቦት 11 ቀን 2008 ዓ.ም የተካሄደ የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 002/2008(ግንቦት 2008 ዓ.ም) | |
| 78 | የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ልማት ምክር ቤት ታህሳስ 05 ቀን 2009ዓ.ም የተካሄደ 3ኛ በደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 003/2009(ታህሳስ 2009 ዓ.ም) | |
| 79 | በከተማ ልማትና ቤቶች መኒስቴር የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተዉ ወደ ስራ ለሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች የሚደራጁበት ዝርዝር የስራ መደቦች(ሀምሌ 2009ዓ.ም) | |